# ትግሉ ይቀጥላል

ሠላም፥ ዴሞክራሲ ላገሬ ብላችሁ
ዱላና፥ አፈናው ሳያሸብራችሁ
ጥቅም ሳይገዛችሁ፥ ለእውነት ቆማችሁ
በወያኔ ጥይት፥ የተገደላችሁ
ለውዷቷ ኢትዮጵያ፥ መስዋዕት የሆናችሁ
እናንተ ብትሞቱም፥ አልሞተም ስራችሁ
ትግሉ ይቀጥላል፥ ታሪክ ያስታውሳችሁ።

የሽፍታዎች ቡድን፥ ለሰው የማይራራ
ግብ ግብ የያዘው፥ ከሰፊው ሕዝብ ጋራ
ከፋፋይ ዘረኛ፥ የከሃዲዎች ጎራ
መውደቂያው ተቃርቧል፥ ደርሷል የሱም ተራ።

እብሪት የወጠረው፥ ጠባብ ትምክህተኛ
ውሸታም፥ ቀጣፊ፥ ቀላማጅ፥ ቀማኛ
የዲያቢሎስ ቁራጭ፥ የጥፋት አርበኛ
ገልብጠን እንጣለው፥ አይጠቅመንም ለኛ።

ደሃ መሃይሙን ሕዝብ፥ የናቁ፥ የጠሉ
ታሪኩን አቃለው፥ ሰንደቁን የጣሉ
በአጥንት ቆጠራ፥ ስጋውን ያደሙ
የኢትዮጵያ ጠላቶች፥ ይድቀቁ ይውደሙ።

እኛስ መስሎን፥ ነበር የምትሻሻሉ
የምርጫውን ውጤት፥ የምትቀበሉ
ሥልጣን ለሰፊው ሕዝብ፥ የምታስረክቡ
በዴሞክራሲ ህግ፥ በደንቡ በአግባቡ።

ለካስ ምንም ቢሆን፥ የእባብ ልጅ እባብ ነው
ጠባይና፥ ባህርይ ዘላለማዊ ነው።

ሥነ ምግባራችሁ አስከፊ ሆነና
መሸነፋችሁን አወቃችሁና
ሥልጣን ማስረከቡ ከበዳችሁና
አሁንም በጡንቻ ተመካችሁና
ማሰር፥ መግደል ሆነ ዛሬም እንደገና።

ክቡር አቶ መለስ የኛ ተራማጅ
ጨካኝ፥ አረመኔ የሰው ዘር አራጅ
የሕዝብ ያገር ፍቅር ጨርሶ የሌለህ
የናዚዎች ቁንጮ፥ የሂትለር ወንድም ነህ።

ለሕዝብ ፀሐይ ወጥቶ ያንተ ቀን ሲመሽ
ጥቅምኛው ፥ ሆዳሙ አጃቢህ ሲሸሽ
ታዛዥህ አምፆ ክብርህ ሲንቋሸሽ
እንደሰባራ ገል ስትንከሻከሽ
ወደ የት ልትገባ፥ ወደ የት ልትሸሽ።

እንያ ንፁህ ዜጎች የጨፈጨፍካቸው
በአጋዚ ጥይት ቢመታ እራሳቸው
በሳንጃ፥ በሰደፍ ቢፈርስ ደረታቸው
ሊገደል አይችልም ቅዱስ ሃሳባቸው
በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ተነስቷል አርማቸው።

በሠፈሩት ቁና መሠፈር አይቀርም
ኢትዮጵያ አትጠፋም ምንም ቢሆን ምንም።

ከሣህሉ በቀለ ቶሮንቶ